## ምድብ አንድ (የሙዓለ ሕፃናት ተማሪዎች)

## 21 ኛ ሳምንት

## ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተመቅደስን አጸዳ

### ዓላማ

- ቤተክርስቲያንን ስለማክበርና በቤተክርስትያን ስለሚፈጸም ሥርዓት መማር

### ምንባባት

- ማቴ.21 እና ዮሐ. 2÷13-22

### መግቢያ

- ልጆች ቤተመቅደስ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ጸሎት የሚደረግበት የእግዚአብሔር ቤት ነው፡፡
- ከድሮ ዘመን ጀምሮ እኛ ዛሬ በቤተክርስትያን እንደምንጸልየው ሰዎች በቤተመቅደስ እየተገኙ ይጸልዩ ነበር ፡፡
- በዛሬው ትምህርታችንም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ቤተመቅደስ ገብቶ ምን እንደአደረገና ሰዎች ቤተመቅደስን እንዴት አለአግባብ እንደተጠቀሙበት እንማራለን፡፡

### ትምህርቱ

- አንድ ቀን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እያስተማረ ወደ እየሩስሳሌም ሄደ፡፡
- በኢየሩስሳሌም ወደ አለው፤ ቤተ መቅደስ ሲገባም÷ ብዙ ሰዎች እንደገበያ ሥፍራ ዕቃ ሲሸጡና ሲለውጡ፣ ተመለከተ፡፡
- የጸሎቱን ቤት የገበያ ቦታ ስላደረጉትም ተቆጥቶ የመሸጫ ጠረጴዛቸውን ሲገለብጥ ሸቀጦችንም ከቤተመቅደስ አወጣ፡፡
- ***"የአባቴ ቤት የጸሎት ቤት ይባላል ተብሎ ተጽፎአል እናንተ ግን የወንበዶች ዋሻ አደረጋችሁት"*** አላቸው፡፡
- ልጆች በቤተክርስቲያን ትጸልያላችሁ? ቤተክርስቲያን የጸሎት ቤት ነው፡፡መላእክት እና ቅዱሳን በቤተክርስቲያን አሉ፡፡
- በተጨማሪም እግዚአብሔር በቤተክርስቲያን የምንጸልየውን ይሰማናል፡፡***"ዓይኖቼና ልቤም በዘመኑ ሁሉ በዚያ ይሆናሉ፡፡"*** 1ኛ.ነገ. 9÷3 ብሏልና ፡፡
- ስለዚህም ቤተክርስቲያንን ስናከብርና ስንጸልይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይደሰትብናል፡፡***"ቤቴ የጸሎት ቤት ነው"*** ብሎናልና፡፡ ማቴ 21÷13

### ጥያቄዎች

1. ቤተመቅደስ ምንድ ነው?
2. ጌታችን ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ በቤተመቅደስ የነበሩት ምን ይሰሩ ነበር?
3. ሕዝቡ በቤተመቅደስ ሲሸጡና ሲለውጡ ጌታችን ኢየሱስ ምን አደረገ?
4. በቤተመቅደስ ምን ማድረግ አለብን?

### ምኩራብ

- ልጆች ይህ ሳምንት በቤተክርስቲያን ምኩራብ ይባላል፤ጌታችን በምኩራብ ማስተማሩም ይታሰባል፡፡ዮሐ.2÷12, ማቴ 4÷23:: ልጆች ምኩራብ ምንድር ነው?

# Cleansing the Temple



***"My house shall be called the house of prayer."*** **Mathew 21:13**

**ይቆየን።**